| | |
|---|---|
| ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ<br>አውቃፍ ሚኒስትር | ጁማዳል ኣኺራ 13/1441 ሂ.<br>ፌብሮሪ 7/2020 ግ. |

**የእምነት ፍሬዎች**

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ يَهْدِيهِمْ رَبُّهُمْ بِإِيمَانِهِمْ تَجْرِي مِنْ تَحْتِهِمُ الأَنْهَارُ فِي جَنَّاتِ النَّعِيمِ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጒም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ጌታቸው በእምነታቸው ምክንያት (የገነትን መንገድ) ይመራቸዋል፡፡ ከሥራቸው ወንዞች ይፈስሳሉ፡፡ በመጠቀሚያ ገነቶች ውስጥ ይኖራሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ዐ.ወ.) ለባሮቹ ከቸራቸው ጸጋዎች አንዱ የሰው ልጅ የሚሥራው መልካም ሥራ በመጨረሻ ደግ ፍሬ እንዲኖረው ማድረጉ ነው፡፡ መልካም ውጤታቸው ግለሰቡንና ማህበረሰቡን ከሚያካትቱ ተላላቅ ሥራዎች በመጀመሪያ የሚጠቀሰው መልካም ሥራ በአላህ (ዐ.ወ.) ማመን ነው፡፡ ሰይዲና ጅብሪል (ዐ.ሰ.) በጠየቃቸው ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሙእሚን ልብ ሊሰፍን ስለሚገባው እውነተኛ እምነት (በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና ደግም ሆነ መጥፎ ማንኛውም ተግባር የአላህ ፍርድ በመሆኑ ማመነህ ነው) ብለዋል፡፡ እሱም እውነትህ ነው አላቸው)፡፡

ይህም የሚጠቁመው እምነት በምላስ የምንናገረው ቃል ሳይሆን በልብ የሚቀረጽ፣ በምላስ የምንገልጸውና በአካላት የምናከናውነው ተግባር መሆኑን ነው ይላሉ ሊቃውንት፡፡ ይህን ማለትም እምነት በልብ የጸናና የአላህን ትእዛዛት በመፈጸምና ከከለከለውም ነገር በመራቅ በተግባር የሚከናወን ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡

ሐሰን አል በስሪ የተሰኙት ሊቅ አንተ ሙእሚን ነህ ወይ? የሚል ጥያቄ በተሰነዘረላቸው ወቅት እንድህ በማለት ነበር የመለሱት፡ (አምነት ሲባል ሁለት ዓይነት

ነው፡፡ የምትጠይቀኝ በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በጀነት፣ ሙቶ በመነሳትና በሒሳብ ስለማመን ከሆነ አዎ ሙእሚን ነኝ፡፡ ነገር ግን የምትጠይቀኝ እንድህ ስለሚለው የአላህ ቃል ከሆነ፡

{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَاناً وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ * الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلاَةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنْفِقُونَ * أُولَئِكَ هُمُ الْمُؤْمِنُونَ حَقّاً}

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡እነዚያ ሶላትን ደንቡን አሟልተው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱ ናቸው፡፡ እነዚያ በእውነት አማኞች እነሱ ብቻ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡ በአላህ ይሁንብኝ እኔ ከነሱ አንዱ ልሁን አልሁን የማውቀው ነገር የለኝም፡፡

እውነተኛ እመነት ማለት የልብን ማእከላዊ ክፍል የሚነካና መላ መንፈስን የሚገዛ ሲሆን ጠንካራ ተጸእኖው በመንፈስና በአእምሮ እንድሁም በግለሰቡና በማህበረሰቡ ውጫዊ ገጽታም ይንጸባረቃል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ እውነተኛ እምነት ፍሬዎች አንዱ ለአማኙ የአላህ ባሪያ መልካም ስነ ምግባርን የሚያወርስ መሆኑ ነው፡፡ እምነትና ታማኝነት የማይለያዩ ባለአንድ ስር ሁለት ዛፎች ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ታማኝነት የጎደለው ሰው እምነት የለውም፡፡ ቃሉን የማያከብር ሰውም ሃማኖት የለውም)፡፡ እንድሁም እመነትና የአክብሮት ይሉኝታ የማይለያዩ ጣምራዎች ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የአክብሮት ይሉኝታና እምነት ባንድ ላይ ጣምራዎች ሆነዋል፡፡ አንደኛው በሚወገድበት ወቅት ሌላውም ይወገዳል)፡፡ እምነትና እውነተኛነት የተያያዙ ናቸው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰፍዋን ኢብን ሱለይም የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ሰዎች ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሙእሚን በቅቧቃ ይሆናል ወይ? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸው (አዎን) በማለት መለሱ፡፡ ሙእሚን ንፉግ ይሆናልን? ተብለው ቢጠየቁም (አዎን) አሉ፡፡ ከዚያም ሙእሚን ውሸታም ይሆናል ወይ? ተብለው ተጠየቁ፡፡ እሳቸውም (አይሆንም) በማለት መለሱ፡፡

በርካታ ሊቃውንት እመነትን እውነት ነው በማለት ገልጸውታል፡፡ ሲያብራሩም እውነተኛ እምነት ጉዳት ሊያደርስበት የሚችል መሆኑን ቢገምትም እንኳ አውነትን መናገርና ሊጠቅመው የሚችል መሆኑን ቢገምትም እንኳ ሀሰትን ከመናገር መታቀብ ነው ይላሉ፡፡ በመልካም ምግባር የታነጸ ሰው ብታገኝ ይህ የእውነተኛ እመነት ፍሬ መሆኑን እወቅ፡፡ ወደወነት አዘንባዩ ሃይማኖታችን የመልካም ምግባር፣ የማበጀት፣ የግንባታና የልማት ሃይማኖት ነው፡፡ ከዚህ የሚጨምር ሰው ካየህ ከሃይማኖት ደንቦች ውጭ ባእድ ነገር የጨመረ መሆኑን እወቅ፡፡

ከአምነት ፍሬዎች ሌላው ደግሞ ቀስታና መረጋጋት ነው፡፡ እመነት በአንድ ሰው መንፈስ ውስጥ በሚመቻችበት ወቅት ያን ጊዜ መንፈሱ በርጋታ፣ በእርግጠኝነትና

በርካታ ትሞላና በዚህች ዓለምና በመጨውም ዓለም ተደሳች ትሆናለች፡፡ እውነትኛ ሙእሚን ከደረሰበት መከራ በምን ዓይነት ሊያመልጥ የማይችል እንድሁም ያ ከሱ ያመለጠው መከራ በምን መልኩ ሊደርስበት የማይችል መሆኑን በእርግጠኝነት ያውቃል፡፡ በመሆኑም በደስታ ጊዜ ከሚያደርሰው የምስጋና ደረጃ በስቃይ ጊዜ ወደትእግስት ደረጃ ይሸጋገራል፡፡ ማንኛውም አላህ በሱ ላይ የፈረደበት ነገር ለሱ ደግ መሆኑን በመገንዘብ መንፈሱ ትረካለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

﴿وَمَن يُؤْمِن بِاللَّهِ يَهْدِ قَلْبَهُ﴾

ትርጉሙም (በአላህም የሚያምን ሰው ልቡን (ለትዕግስት) ይመራዋል...) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የሙእሚን ነገር የሚገርም ነው፡፡ ነገሩ ሁሉ ለሱ መልካም ነው፡፡ ያም ነገር ለሙእሚን ብቻ እንጂ ለማንም አይሆንም፡፡ እሱ ደስታ ቢያጋጥመው ያመሰግናል፡፡ ያም ለሱ መልካም ነገር ነው፡፡ መከራም ቢደርስበት ይታገሳል ያም ለሱ መልካም ነገር ነው)፡፡

ከእምነት ፍሬዎች ሌላው ደግሞ እምነት አማኙነት አጥፊ ኃጢአቶችን እንዳይፈጽም የሚጠብቀው መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ዝሙተኛ ዝሙት ሲፈጽም እሱ አማኝ ሆኖ አይደለም፡፡ አስካሪ ነገር የሚጠጣም እሱን ሲጠጣ አማኝ ሆኖ አይደለም፡፡ ሌባም ሲሰርቅ እሱ አማኝ ሆኖ አይደለም፡፡ ሰዎች እሱን ሲያነሳ ዓይኖቻቸውን ወደሱ እየሰነዘሩ ዘረፋን ሲፈጽምም እሱ አማኝ ሆኖ አይደለም)፡፡

እንደዚሁም እውነተኛ ሙእሚን በማሾፍ፣ በማፌዝና በምጥፎ ጥርጣሬ የሰዎችን ስሜት ከመጉዳት አጥብቆ ይርቃል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَى أَن يَكُونُوا خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَاءٌ مِّن نِّسَاءٍ عَسَى أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ وَلَا تَلْمِزُوا أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُوا بِالْأَلْقَابِ بِئْسَ الِاسْمُ الْفُسُوقُ بَعْدَ الْإِيمَانِ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُولَئِكَ هُمُ الظَّالِمُونَ﴾

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ፡፡ በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፡፡ ከእምነት በኋላ የማመጽ ስም ከፋ፡፡ ያልተጸጸተም ሰው እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اجْتَنِبُوا كَثِيرًا مِّنَ الظَّنِّ إِنَّ بَعْضَ الظَّنِّ إِثْمٌ وَلَا تَجَسَّسُوا وَلَا يَغْتَب بَّعْضُكُم بَعْضًا أَيُحِبُّ أَحَدُكُمْ أَن يَأْكُلَ لَحْمَ أَخِيهِ مَيْتًا فَكَرِهْتُمُوهُ وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ تَوَّابٌ رَّحِيمٌ﴾

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ፤ ከጥርጣሬ ከፊሉ ኃጢአት ነውና፡፡ ነውርንም አትከታተሉ፡፡ ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ፡፡ አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? (ሙብላቱን) ጠላችሁትም፤ (ሐሜቱንም ጥሉት)፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{لَّوْلَا إِذْ سَمِعْتُمُوهُ ظَنَّ الْمُؤْمِنُونَ وَالْمُؤْمِنَاتُ بِأَنفُسِهِمْ خَيْرًا وَقَالُوا هَٰذَا إِفْكٌ مُّبِينٌ} .

ትርጉሙም ((ውሸቱን) በሰማችሁት ጊዜ ምእምናንና ምእምናት በነፍሶቻቸው ለምን ደግን ነገር አልጠረጠሩም ለምንስ ይህ ግልጽ ውሸት ነው አላሉም..) ማለት ነው፡፡

ድጋፍና ድል ሌላው የእምነት ፍሬ ነው፡፡ እውነተኛ እምነት አንድን ባሪያ ዘወትር ከአላህ ጋር እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَنَّ اللَّهَ مَعَ الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም ( አላህም ከምእምናን ጋር ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِن تَنصُرُوا اللَّهَ يَنصُرْكُمْ وَيُثَبِّتْ أَقْدَامَكُمْ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን (ሃይማኖቱን) ብትረዱ፤ ይረዳችኋል፡፡ ጫማዎቻችሁንም ያደላድላል፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{إِنَّا لَنَنصُرُ رُسُلَنَا وَالَّذِينَ آمَنُوا فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَيَوْمَ يَقُومُ الْأَشْهَادُ}

ትርጉሙም (እኛ መልክተኞቻችንን፣ እነዚያንም ያመኑትን በቅርቢቱ ሕይወት ምስክሮችም በሚቆሙበት ቀን በእርግጥ እንረዳለን፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡

{وَكَانَ حَقًّا عَلَيْنَا نَصْرُ الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም( ምእመኖቹንም መርዳት በእኛ ላይ ተገቢ ሆነ፡፡) ማለት ነው፡

{الَّذِينَ قَالَ لَهُمُ النَّاسُ إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُواْ لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ إِيمَاناً وَقَالُواْ حَسْبُنَا اللّهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ فَانقَلَبُواْ بِنِعْمَةٍ مِّنَ اللّهِ وَفَضْلٍ لَّمْ يَمْسَسْهُمْ سُوءٌ وَاتَّبَعُواْ رِضْوَانَ اللّهِ وَاللّهُ ذُو فَضْلٍ عَظِيمٍ} .

ትርጉሙም(እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፡- «ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው» ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው «በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ!» ያሉ ናቸው፡፡ ከአላህም በኾነ ጸጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ኾነው ተመለሱ፡፡ የአላህንም ውዴታ ተከተሉ፤ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡) ማት ነው፡፡

ከእምነት ፍሬዎች ሌላው ደግሞ አላህ (ዐ.ወ.) የዚያን የሙእሚን ባሪያውን ውዴታ በፍጥረታቱ ዘንድ የሚያሰፍን መሆኑ ነው፡፡ ትክክለኛ ሙእሚን ልዝብ፣ ሰዎችን የሚለምድና እነሱም የሚለምዱት መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጹኣል፡

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ سَيَجْعَلُ لَهُمُ الرَّحْمَنُ وُدًّا}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና በጎ ሥራዎችን የሠሩ አልረሕማን ለእነሱ ውዴታን ይሰጣቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡

አንድ እውነተኛ ሙእሚን በንጹህ ልቡ ወደአላህ (ዐ.ወ.) ከዞረ አላህ በቀጥታ የሚቀበለው መሆኑን ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ባወሩት የቁድስ ሐዲስ እንድህ ሲሉ አብራርተዋል፡ (አላህ አንድን ባሪያ ሲወደው ጅብሪልን ይጠራና አላህ እገሌን ይወደዋልና ዉደደው ይለዋል፡፡ ጅብሪልም ይወደዋል፡፡ ጀብሪልም በሰማይ ነዋሪዎች ዘንድ አላህ እገሌን ይወደዋልና ውደዱት ሲል ጥሪ ያስተላልፋል፡፡ የሰማይ ነዋሪዎችም ይወዱታል፡፡ ከዚያም በምድር ለሱ ቅቡልነትን ይቸረዋል፡፡ በሌላ ቁድስ ሐዲስም እንድህ ይላሉ፡ (በሪያዬ ዘወትር በፈቃዱ በሚያደርሳቸው ዒባዳዎች ወደኔ አይቃረብም በዚያ ጥረቱ የምወደው ብሆን እንጂ፡፡ ከወደድኩትም የሚሰማበት መስሚያው፡ የሚያበት ማያው፣ በሱ የሚሠራበት እጁና በሱ የሚራመድበት እግሩ እሆነዋለሁ)፡፡

ችግር መወገድና መከራ መነሳትም ሌላው የእምነት ፍሬ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እነድህ ይላሉ፡ (እኔ በአንድ ሰው ላይ ጭንቀት ወይም ከዚህች ዓለም መከራዎች አንዱ በሚደርስበት ጊዜ በሱ አላህን ሲጸልይ አላህ መፍትሄ የሚሰጥበትን ነገር አልነግራችሁም ወይም? ) ሰዎችም እሺ ነገሩን አሉ፡፡ እሳቸውም (የአሳው ባለቤት ጸሎት ነው፡፡ አሉና፡

{لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ سُبْحَانَكَ إِنِّي كُنْتُ مِنْ الظَّالِمِينَ}

ትርጉሙም (ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ጥራት ይገባህ፡፡ እኔ በእርግጥ ከበዳዮቹ ነበርኩ .. ፡፡ የምትለዋን አንቀጽ ጠቀሱና አላህ አንድህ ብሏል አሉ፡

{فَاسْتَجَبْنَا لَهُ وَنَجَّيْنَاهُ مِنَ الْغَمِّ وَكَذَلِكَ نُنجِي الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም(ለርሱም ጥሪውን ተቀበልነው። ከጭንቅም አዳነው። እንደዚሁም ምእመናንን እናድናለን።) ማለት ነው። ይህ ጸሎትና የአላህ መቀበለም ለመላ ምእምናን አላህ የፈረደው ጸጋ ነው።

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ።

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው። የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ።

**ሙስሊም ወንድሞች**

ከእመነት ደጋግ ፍሬዎች እጅጉን ታላቁ የማህበራዊ ሰላምና ደህንነት የሚያረጋግጥ መሆኑ ነው። አንድ ትክክለኛ ሙእሚን እመነት በልቡ ሙሉ ለሙሉ ሲሰርጽ የደህንነት፣ የሰላምና የመረጋጋት ምንጭ ሰለሚሆን ሰዎች በሐይወታቸውም ሆነ በንበረታቸው ሙሉ እምነት ይጥሉበታል። ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሙስሊም ማለት ሰዎች በምላሱም ሆነ በእጁ ከሱ በኩል ምንም ተንኮል የማያገኛቸው የሆነ ሰው ነው። ሙእሚን ማለትም ሰዎች በገንዘባቸውም ሆነ በክብራቸው እምነት የሚጥሉበት የሆነ ሰው ነው)።
የእስልምና እምነት ተከታይ ባይሆኑምንኳ በሰላም የሚኖሩን ሰዎች ሰላም ማደፍረስና በነሱም ላይ ጥቃት መሰንዘር የሙእሚን ጸባይ አይደለም። ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ቃል የተጋባን ሰው የገደለ ሰው የጀነትን ጠረን አያገኝም። ጠረኗ ከአርባ ዓመት ርቀት ባሻገር የሚሸት ሆኖ ሳለ።
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጎረቤቱን የሚጎዳና ጎረቤቱ ተርቦ እያለ ጠግቦ ያደረ ሰው እምነት የሌለው መሆኑን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (በአላህ ይሁንብኝ አላመነም በአላህ ይሁንብኝ አላመነም በአላህ ይሁንብኝ አላመነም አሉ)። ሰዎችም እሱ ማነው ሲሉ ጠየቁ። እሳቸውም (ጎረቤቱ ከተንኮሉ የሚፈራ የሆነ ሰው) አሉ። አንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (አጠገቡ ያለ ጎረቤቱ የተራበ መሆኑን እያወቀ ጠግቦ ያደረ ሰው በኔ አላመንም)። ትክክለኛ እመነት የሚባለው ያ መልካም ለመስራት እንድሁም ሌሎችን ለማገዝ የሚገፋፋ የሆነው እምነት ነው። እሱም የባለቤቱን ጸባይ ያሳምራል የአላህን ወዴታ በመፈለግ በእዝነትና ርህራሄ የተሞላው የፍጥረታት ጋር ግንኙነቱ መልካምነትም ጎልቶ ይታያል። አላህ (ሱ.ወ.) እንደህ ይላል፡

**{وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَى حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا * إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنْكُمْ جَزَاءً وَلَا شُكُورًا}.**

ትርጉሙም (ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ። «የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው። ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም።) ማለት ነው።
ሌላው ታላቁ የእምነት ፍሬ ደግሞ በመጭው ዓለም አላህ (ሱ.ወ.) ለምእምናን ባሮቹ ያሀጋጀው ታላቅ ምንዳና ዘላቂው ጸጋ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ يَهْدِيهِمْ رَبُّهُم بِإِيمَانِهِمْ تَجْرِي مِن تَحْتِهِمُ الْأَنْهَارُ فِي جَنَّاتِ النَّعِيمِ}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ጌታቸው በእምነታቸው ምክንያት (የገነትን መንገድ) ይመራቸዋል። ከሥራቸው ወንዞች ይፈስሳሉ። በመጠቀሚያ ገነቶች ውስጥ ይኖራሉ።) ማለት ነው።

{وَبَشِّرِ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ أَنَّ لَهُمْ جَنَّاتٍ تَجْرِي مِنْ تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ}

ትርጉሙም (እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችንም የሠሩትን ለነርሱ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ያሏቸው መኾኑን አብስራቸው። ) ማለት ነው።

{وَالَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ أُولَئِكَ أَصْحَابُ الْجَنَّةِ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ}

ትርጉሙም (እነዚያም ያመኑት በጎ ሥራዎችንም የሠሩት እነዚያ የገነት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ናቸው። ) ማት ነው።

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ إِنَّا لَا نُضِيعُ أَجْرَ مَنْ أَحْسَنَ عَمَلًا}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችንም የሠሩ እኛ ሥራን ያሳመረን ሰው ምንዳ አናጠፋም።) ማለት ነው።

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَانَتْ لَهُمْ جَنَّاتُ الْفِرْدَوْسِ نُزُلًا * خَالِدِينَ فِيهَا لَا يَبْغُونَ عَنْهَا حِوَلًا} .

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው። በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ከእርሷ መዛወርን የማይፈልጉ ሲኾኑ፤ (መስፈሪያቸው ነው)። ማለት ነው። ነብያችን (ሱ.ወ.) አላህ በመጭው ዓለም ለደጋግ

ባሮቹ ዓይን አይቶት የማያውቅና በማንኛውም ሰው ልብ ውል ብሎ የማያውቅ ነገር ማዘጋጀቱን ገልጸው የሚከተለውን አንቀጽ አንብበዋል፡

{فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ أُخْفِيَ لَهُمْ مِنْ قُرَّةِ أَعْيُنٍ جَزَاءً بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ } .

ትርጉሙም (ይሠሩትም በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም፡፡) ማለት ነው፡፡

እኛ ሁላችንም መተዛዘን፣ መተባበርና የአክብሮት ይሉኝታ የተሞላ እምነት እውን ማድረግ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ ከሀሰት፣ ከማታለል፣ ከክህደት፣ ከሀሜትና ከበደል ልንርቅ ይገባል፡፡ የማንኛውንም ሰው ህይዎትና ንብረት መጠበቅ፣ የሀገረንም ክብር ማስከበር ይጠበቅብናል፡፡

ጌታችን ሆይ እምነትን እንድንወድ አድርገን በልባችንም አውበው፡፡ ክህደትን፣ ብልሹነትንና አመጽን እንድንጠላ አድርገን፡፡ ቅንን መንገድ ከሚከተሉትም እድርገን፡፡ ሀገራችንንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡